# የኢትዮጵያ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ

## ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወጣ

## መመሪያ



ግንቦት/ 2013ዓ.ም

## መግቢያ

በኢፌዴሪ ህገ መንግስትና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች መሠረት ማንኛውም ሰው በነፃነት የመማር፤ መልካምና ምቹ የመማሪያና የስራ አካባቢ የማግኘት መብት አለው፡፡

የጾታዊ ጥቃት ተግባር በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን ፣ በተለይ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑት ሴቶች በመሆናቸው ትምህርታቸውን ከወንዶች እኩል በመከታተል ውጤታማ እንዳይሆኑና ሀገራዊ ኃላፊነታቸውንም እንዳይወጡ እንቅፋት መሆኑን አያጠያይቅም

ጾታዊ ጥቃት የሰብአዊ መብት ጥሰት በመሆኑ፤ በተለይም በትምህርት ተቋማት አካባቢ እየተፈፀመ ያለው የጾታዊ ትንኮሳ ተግባር ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዳይኖር እንቅፋት እየሆነ በመምጣቱና በተለይም የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ ብቃትና ውጤታማነትን የሚያዳክም በመሆኑ፣ የጾታዊ ጥቃት ተግባራትን ለመከላከልና ለመቀነስ ፣ ተፈፅሞ ቢገኝ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የውስጥ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ይህንን የውስጥ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### አንቀፅ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የኢትዮጵያ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ» ጾታዊ ጥቃትን ለመከላከል የወጣ የውስጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

**2.1. «ጾታዊ ጥቃት»** ማለት ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከሌላኛው ፈቃድ ውጪ የሚፈፀም ወሲባዊ፣ጾታን መሰረት ያደረገ ሞራላዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካላዊ ወዘተ ይዘት ያለው በሌላው ግለሰብ ላይ ጉዳትን የሚያስከትል ድርጊት ነው፡፡

**2.2.** «**የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ» ማለት፣** በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በማንኛውም ፕሮግራም ትምህርት የሚከታተሉ ሠልጣኞች፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ መምህራንና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ ሁሉንም ሰራተኞች ማለት ነው፡፡

**2.3. «ፕሬዝዳንት» ማ**ለት ዩኒቨርሲቲውን በበላይነት እንዲመራ የተመደበ ሀላፊ ማለት ነዉ፡፡

**2.4 «የበላይ ኃላፊ»** ማለት ዩኒቨርሲቲውን በከፍተኛ አመራር ደረጃ በበላይነት የሚመሩ ኃላፊዎች ማለት ነው፡፡

**2.5. «የማህበራዊ አገልግሎት ቅጣት»** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) (ሐ) መሠረት ቀላል የጾታዊ ጥቃት ተግባር በፈፀመ ሠልጣኝ እና ሰራተኛ ላይ የሚፈፀም የቅጣት አይነት ሲሆን፣ ቅጣቱ የዩኒቨርሲቲው መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር የአካባቢ ፅዳት፣ አትክልት መንከባከብ እና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡

**2.6 «ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተቋቋመው የጾታዊ ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ነው፡፡

**2.7 «ተገቢው ጥበቃ»** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የኮሚቴ አባል ሆኖ እንዲሰራ ለተመደበ ወይም ክስ ላቀረበ ወይም ምስክርነት ለሰጠ ሰልጣኝ፤ የተቋሙ ማህበረሰብ የሚሰጥ ጥበቃ ሆኖ የሚከተሉትን እርምጃዎች ያካትታል፤

- ሀ. ጥበቃ የሚያስፈልገው ሰልጣኝ በሆነበት ጊዜ አሰልጣኙ /የመማሪያ ክፍሉ እንዲለወጥለት ወይም ፈተናውና የተግባር ልምምድ ምዘናዉ በሌላ አራሚ እንዲታረምለት እና እንዲታይለት ማድረግን፣
- ለ. ጥበቃ የሚያስፈልገው መምህር ወይም የአስተዳደር ሰራተኛ ከሆነ የስራ ሃላፊው እንዲቀየርለት ወይም ወደ ሌላ የስራ ክፍል ወይም የስራ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከነዚህ እርምጃዎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሌላ ተገቢነት ያለው ከለላ፣የሚያካትት ነው፡፡

**2.8.** በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፁት ቃላት ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀፅ 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለሚፈፀሙ የጾታዊ ጥቃት ተግባራት ፈፃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# የጾታዊ ጥቃት አይነቶች

### አንቀፅ 4· የጾታዊ ጥቃት ተግባራት አይነቶች

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.1 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የጾታዊ ጥቃት ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፣

## አንቀፅ4.1 ቀላል የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች፣

1. አስነዋሪ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ አካላትን አጋልጦ ማሳየት፣
2. ፅሁፎችና መጽሔቶችን በመጠቀም በትምህርት ተቋማት ውስጥ የአንድ ሰው ፆታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስ በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ በማስደገፍ ያለአንዱ ወገን ፈቃድ ለሌላ ሰው ማሣየት ወይም ማስተላለፍ
3. ጾታን መሰረት አድርጐ ማጥላላት ማንኳሰስ ማለትም አካላዊ ፣ ሥነልቦናዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርሱ ተግባራትን መፈፀም
4. ነቀፌታ ያልተፈለጉና ኢሞራላዊ መገለጫዎችን ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን መጠቀም

## አንቀፅ 4.2 ከባድ የጾታዊ ጥቃት ዓይነቶች፣

1. ቀላል የጾታዊ ጥቃት በመፈፀም በተወሰደበት የቅጣት እርምጃ ባለመታረም በድጋሚ ቀላል የጾታዊ ጥቃት መፈፀም፣
2. በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ፣ በድህረ ገፅ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ምስል በመጠቀምና በማስመሰል የሌላን ሰው

ወሲባዊ ሕይወት የሚያጋልጡና የሚያንቋሽሹ ተግባራትን መፈጸም፣

3. አንድን ሰው በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ጾታን መሰረት አድርጐ በመከታተል እና በነፃነት የመንቀሳቀስ መብትን በመጋፋት ላይ የስነልቦና ጫና ማሳደር፣

4. ለትምህርት ውጤትም ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራት ወሲብን እንደ ቅድመ

ሁኔታ አስቀምጦ መጠየቅ፣

5.. ወሲብ አዘል ድርጊቶችን በማስገደድ ለመፈፀም በማሰብ የትምህርት

መሣሪያዎችና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማትና መደበቅ፣

6. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን የጾታዊ ጥቃት አይነቶች እንዲፈጸም የተባበረ

ወይም ያደመ፡፡

7. በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም ቀላል ጾታዊ ጥቃት በከባድ ጾታዊ ጥቃት

ተግባራት ከተመለከቱት የጥፋት ድርጊቶች ጋር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል፡፡

8. አስገድዶ የደፈረ

9. ከላይ የተገለፁትንና ይህንን መሰል ድርጊቶች በፈፀመ የዩኒቨርሲቲው

ማህበረሰብ እና ሰራተኛ ላይ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## አንቀፅ 5. የሚወሰዱ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች፣

ማንኛውም ሰልጣኝ፤ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የጾታዊ ጥቃት አይነቶች ከፈጸመ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት የቅጣት አይነቶች አንዱ ተፈጻሚ ይደረግበታል፡፡

1. በሠልጣኞች ላይ የሚወሰድ ቀላል የሥነ ሥርዓት እርምጃ፣

   ሀ· የቃል ማስጠንቀቂያ፣
   ለ· የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
   ሐ· የማህበራዊ አገልግሎት ቅጣት እንዲሰጥ ማድረግ፣

2. በሠልጣኞች ላይ የሚወሰድ ከባድ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣

   ሀ· ለአንድ ሴሚስተር ከትምህርት መታገድ፣
   ለ· ለአንድ አመት ከትምህርት መታገድ፣
   ሐ· ዕጩ ተመራቂ ሲሆን የትምህርት ማስረጃን ከ 3 ወር እስከ አንድ ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ማገድ፣
   መ. እጩ ተመራቂው የትምህርት ማስረጃው አይሰጠውም

3. በዩኒቨርሲቲው መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች ላይ የሚወሰድ ቀላል የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣

   ሀ· የቃል ማስጠንቀቂያ፣
   ለ· የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
   ሐ· እስከ 2 ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፣

4. በዩኒቨርሲቲው መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኛ ላይ የሚወሰድ ከባድ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ፣

   ሀ· የሦስት ወር ደመወዝ መቀጮ፣
   ለ. ካለበት የስራ ወይም ደመወዝ እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ፣
   ሐ· ከሥራ ማሰናበት፣

# ክፍል አራት

## አንቀፅ 6· ሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ፣

1. በዩኒቨርሲቲው ያሉ ማህበረሰብ ላይ የሚፈፀም ጾታዊ ጥቃትን አጣርቶ የውሣኔ ሃሣብ ለተቋሙ ፕሬዝዳንት የሚያቀርብ የጾታዊ ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
2. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚፈፀም የጾታዊ ጥቃት ጉዳዮች በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የዲስፒሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 77/2002 መሠረት የተቋቋመው የጾታዊ ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ አጣርቶ የውሣኔ ሀሳቡን ለበላይ ኃላፊው አቅርቦ ያስወስናል፡፡
3. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚገኙ ሠልጣኞች ላይ የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት የሚቀርበው ለተማሪዎች ዲን ሆኖ የተማሪዎች ዲን ክሱን ለአጣሪ ኮሚቴው አቅርቦ ውሣኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል

4. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚገኙ መምህራን ላይ የሚደርስ ጾታዊ ጥቃት ክስ የሚቀርበው ለመምህራን ማህበር ተወካይ ሆኖ የመምህራን ማህበሩ ተወካይ ክሱን ለአጣሪ ኮሚቴው አቅርቦ ውሣኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል

5. ጉዳዩን በበላይነት እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው አካል ተከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ኮሚቴው ጉዳዩን አጣርቶ በሚቀጥለው እርከን ካለው የበላይ አካል ከውሣኔ አስተያየት ጋር ያቀርባል፡፡

6. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ ማናቸውም ዓይነት ውሣኔዎች አቤቱታ አቅራቢውን ጉዳዩ በሌሎች ሕጎች የተቀመጡ መደበኛ የፍርድ ሂደቶችን እንዳይከተል አያግዱትም፡፡

# ክፍል አምስት

## አንቀፅ 7· የጾታዊ ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ አወቃቀር፣

1. የጾታዊ ትንኮሳ አጣሪ ኮሚቴ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የኮሚቴው አባላት፣

   ሀ· የዩኒቨርሲቲው ሴት ተማሪዎች ፎረም ተወካይ /የተማሪ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ/

   ለ· የዩኒቨርሲቲው የስርዓተ-ፆታ ዳይሬክቶሬት ተወካይ፣

   ሐ· የተማሪ መማክርት ኃላፊ/ተወካይ፣የተማሪዎች ፕሬዝዳንት /የተማሪ ጉዳይ በሚታይበት

   መ· የዩኒቨርሲቲው መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ተወካይ፣

   ሠ· በአስተዳደር ሠራተኞች የሚመረጥ አንድ ተወካይ፣

   ረ. የተማሪዎች ዲን/ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር/ተወካይ

   ሰ· በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚወከል አንድ ሰብሳቢ

3. የኮሚቴው አወቃቀር የፆታ ስብጥርን ያማከለ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 8. የአባላት መመዘኛ፣

ማንኛውም የኮሚቴ አባል፣

1. በመልካም ስነ-ምግባር የተመሰገነ፣
2. በጾታዊ ጥቃት ተግባር ተከሶ ወይም ጥቃት ፈጽሞ ያልተቀጣ፣
3. ቢያንስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለአንድ ዓመት ያገለገለ፣

   መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ 9· የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር፣

1. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የጾታዊ ጥቃት ድርጊት ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት የመመርመርና የውሣኔ ሃሣብ የማቅረብ፣

2. ኮሚቴው አቤቱታዎችን ሲመረምር አቤቱታ አቅራቢን፣ተከሳሽን ወይም ምስክሮችን የመጥራትና የመስማት፣ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች እንዲቀረቡለት የማዘዝ ወይም ሰነዱ ባለበት ቦታ ሄዶ የማየትና ሌሎች ለምርመራ ተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ፡፡

## አንቀፅ 10· የስብሰባ ሥነ-ስርዓት

1. ኮሚቴው የዩኒቨርሲቲው የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት የቀረቡ አቤቱታዎችን አስቸኳይነት መሠረት በማድረግ በሚያቀርበው ጥያቄ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

2. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሣኔ ሃሣብ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ ድምፅ እኩል በኩል የተከፈሉ እንደሆነ የሰብሳቢው ወይም የተወከለ ሰብሳቢ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

3. ኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤን ጨምሮ ሌሎች የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶች የፌዴራል መንግስት የዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት ደንብ ቁጥር 77/2002 የተከተለ ይሆናል፡፡
4. የኮሚቴው ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ በሰብሳቢው በፅሁፍ የተወከለ ሌላ አባል ስብሰባውን ሊመራ ይችላል፡፡

5. በኮሚቴው የሚጣሩ አቤቱታዎች የመጨረሻ ውሣኔ አግኝተው በደብዳቤ እስኪገለፅ ድረስ በሚስጥር መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ11· የኮሚቴ አባላት መከተል ስለሚገባቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች፣

1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴ አባልነት ያወቃቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች በሚስጥር መጠበቅ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል የቀረቡ አቤቱታዎች ከራሱ፣ ከቅርብ ጓደኛው ወይም ከዘመዱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ከአባልነት እራሱን ማግለል አለበት፡፡

3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል አቤቱታዎችን በሚያይበት ወቅት በፆታ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ መሠረት ያደረጉ አድሎን መፈፀም አይኖርበትም፡፡

4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች ከኮሚቴው የሚጠበቁ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የጣሰ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚቴውን ሥራ ያደናቀፈ የኮሚቴ አባል ከአባልነቱ መሠረዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲስፕሊን ጉድለት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ12· የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፣

1· ማንኛውም ጾታዊ ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ጉዳዩ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አንድ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ካልቻለ ተቀባይነት ያለው ህጋዊ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

2. የአቤቱታ ማመልከቻ መያዝ ስለሚገባቸው ዝርዝሮች፣

ማንኛውም የአቤቱታ ማመልከቻ፣

ሀ. የከሳሽ ስም

ለ. የሚማመርበት የትምህርት ክፍል ወይም የሚሰራበት ክፍል

ሐ. ድርጊቱ የተፈፀበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት

መ. ተፈፀመ የተባለው የጾታዊ ትንኮሳ ዓይነት/የድርጊቶ መገለጫዎች

ሠ. የትንኮሳው ፈፃሚ ስምና የትምህርት ክፍል/የሥራ ቦታ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ

ረ. የምስክሮች ስም

ሰ. በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍም ሆነ ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ

ቀ. የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበትን ቀን መያዝ ይኖርበታል፡፡

4. በዩኒቨርሲቲው ሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች የያዘ የአቤቱታ ማመልከቻዎች የሚቀርቡባቸው ቅጾች ማዘጋጀት አለበት፡፡

## አንቀፅ13. አቤቱታ ማቅረብ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች

1. በአንቀጽ 12 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 የተጠቀሰው የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ፣
2. ቀደም ሲል ጉዳዩ በዚሁ አካል የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ፣
3. ተከሣሹ ከተቋሙ ጋር ያለውን ግንኙነት ካቋረጠ በኋላ

## አንቀፅ14. አቤቱታ የቀረበበት ሰው የመደመጥ መብት፣

1. ማንኛውም ጾታዊ ጥቃት ተግባር አቤቱታ የቀረበበት ሰው የቀረበበትን አቤቱታ የማወቅ፣ ራሱን የመከላከልና የመደመጥ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
2. ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ከቀጠሮ 10 ተከታታይ ቀናት በፊት አቤቱታ ለቀረበበት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

## አንቀፅ15. የሥርዓት-ጾታ ኮሚቴ የምርመራ ሪፖርት አቀራረብ፣

1. ኮሚቴው አቤቱታ በቀረበለት በ20 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ የውሣኔ ሃሣቡን ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡
2. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የምርመራ አስተያየቱን በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡
3. የበላይ ኃላፊው ከኮሚቴው የቀረበለትን የምርመራ ሃሣብ ለማጽናት ወይም ለመሻር ወይም ለማሻሻል ወይም ከኮሚቴው የውሣኔ ሃሣብ የተለየ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በአቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሃሳብ ከማቅረቡ በፊት የጾታዊ ጥቃት እንዲቆም የሚያደርገው ጊዜያዊ ትዛዞች ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀፅ16. ይግባኝ

1. በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 75 ለአስተዳደር ሠራተኞች የተቀመጠው የይግባኝ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጾታዊ ጥቃት የተከሰሰና የተቀጣ ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የበላይ ኃላፊው የቅጣት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ቀጥሎ ላለው የሥልጣን እርከን ማቅረብ ይችላል፡፡

2. ይግባኝ ሰሚው ይግባኙ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይግባኙን መርምሮ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

### አንቀፅ17. **የቅጣት ሪኮርድ መቆያ ጊዜ**

1. ቀላል የጾታዊ ትንኮሳ የፈፀመና የተቀጣ ሰው የጥፋት ድርጊቱን ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ለሁለት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል፡፡
2. ከባድ የጾታዊ ጥቃት የፈፀመና የተቀጣ ለአራት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል፡፡

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ18. ስለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች

የተለያዩ ስራዎች ለመስራት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል የሚገቡ የስራ ተቋራጮች ወይም ግለሰቦች፣ ለአጫጭር ስልጠና የሚገቡ ሠልጣኞች ዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዳይተላለፉ በሚገቡት ግዴታ ላይ እንዲካተት መደረግ አለበት፡፡

### አንቀፅ19. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የጾታዊ ጥቃት መፈፀሙን ባወቀ ጊዜ ሪፖርት የማድረግ፣ለምስክርነት ሲጠራ የመቅረብ፣በግል ሆነ በሥራ ኃላፊነቱ የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት የመተባበር ኃላፊነት አለበት፡፡

### አንቀፅ20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከሰኔ/2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡